**ሐዲስ ሐዋርያ**

ሐዲስ ሐዋርያ ተክለ ሃይማኖት

በብርሃን መስቀሉ አሰጠን በረከት

በአማላጅነትህ ይታደለን ጸጋ

ሁሉን ከሚችል አልፋና ኦሜጋ

አዝ . . . . . .

የሥላሴ መዝገብ የምስጢር ሰሌዳ

ተጽፎብህ ያለ የምስጋና ጋዳ/እጅ መንሻ/

አንተ ታላቅ መሪ እውነተኛ እረኛ

ለኢትዮጵያ ጴጥሮስ ነህ ለበጎቹ ዳኛ

አዝ . . . . .

የምንጠጣው ውኃ የምንበላው ምግብ

ተበክሏልና በዘንዶ በእባብ

በመስቀሉ ባርከው መርዝነቱ ይጥፋ

ቀናዒው ተክለ አብ የሁላችን ተስፋ

አዝ . . . . . .

የትሕትና አባት የጽድቅ መምህር

እጅግ የበዛ ነው የተሰጠህ ክብር

መከራና ችግር ሲገጥመን ኀዘን

ፈጥነህ ድረስና በክንፍህ ጋርደን

አዝ . . . . . .

ከአምላክ ተሰጠህ የጽድቅ አክሊላት

በሞትህም ከበርክ አገኘህ ዕረፍት

እኛንም በምልጃህ አግባን ገነት